ሠ/አስተማሪዎች፤ የኢትዮጵያ አስተማሪ፤ሴክተር ሪቪው የተባለው፤ የድሃ ልጅ እንዳይማር
የወጣውን ሕግ በመቃወም እንዳሳየከው ቁርጠኝነትና አስተዋይነት ሁሉ
ፋሺሽታዊውን ዓዋጅ ለሕዝብ በደንብ እንዲገባ አድርግ፡፡ይህ ዓዋጅ ሥራ ላይ እስካለ ድረስ
በ'እድገት በኅብረት' ዘመቻ አትካፈል፡፡

ረ/የመንግሥት ሠራተኞች፤ፋሺሽታዊ ዓዋጅ ከማወጁ ሌላ፤ወታደራዊው መንግሥት ካሁኑ ባሥንት ጀምር
የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፤ምንም ዓይነት የሥራ ዕውቀት በሌላቸው የጎታደር
መኰንኖች እንዲመሩ ተወስኗል፡፡ይህ ጥንቱንም የቆረቆዘው ኢኮኖሚና በጠቅላላው በአገሪቱ ላይ
የሚያስከትለው ችግር ከአንተ የተሰወረ አይደለም፡፡በየመሥሪያ ቤትህ ተወያይ፤ተደራጅ፤ሥራ
የማቆም አድማ ለማድረግ ተዘጋጅ፡፡

ሰ/ነጋዴዎች፤ይህ ወታደራዊ መንግሥት፤እውነተኛ ለውጥ አስገኝቶ ከውጭ አገር ከበርቴዎች
አለጠበቃችሁም፡፡ገለጸ በሆኑ ሕጎች ላይ የተመሠረተ ዋስትና አለሰጣችሁም፡፡
በላዩ ላይ ደግሞ ፋሺሽታዊ ዓዋጆችን ጫነባችሁ፡፡መብታችሁንና ጥቅማችሁን ለማስከበር ተደራጁ፤
ተዘጋጁ፡፡

ሸ/የተጨቆናችሁ ብሔሮች ሕዝቦች፤ ተጨቆንን ማለት፤እኩልነትንና ፍትሕን መጠየቅ የሚያሳስርና
የሚያስገድል ወንጀል ነው ብሏችኋል ወታደራዊው መንግሥት፡፡
ትግላችሁን ከሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ጋር በማቀነባበርና በማስተባበር ለእኩልነታችሁና
ለመብታችሁ ታገሉ፡፡

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ሠ ፊ ው ሕ ዝ ብ ሆ ይ ፤

ብዛት ያንተ ነው
ሥራ ያንተ ነው
ጊዜውም ያንተው ነው ፤ ሌሎች ግን ጊዜ
የጣላቸው፤ታሪክን ለማቆም የሚቃጡ፤ወደ ኋላ ለመመለስ የሚፈልጉ ያለፈበት፤ያፈጀበት ዘመን
ርዝራዦች ናቸው፡፡ አንድነትህ ከጠበቀና ቆርጠህ ከተነሣህ ድልህ አያጠራጥርም፡፡

ፋሽዝም ይውደም

የሠፊው ሕዝብ የትግል አንድነት ይጠንክር

ሕዝብ ያቸንፋል